# በጥይት የወጉትን በመጽሀፍ ወግ?

ታሪኩ አባዳማ ጥር 2004

የመጣጥፌ አጠቃላይ ትኩረት በቅርቡ ታትመው በወጡት የ‘በረከት ስምዖን’ እና መንግስቱ ሃ/ማርያም መፃህፍት ዙርያ ይሆናል። ‘በረከት’ን በክፊል ትምህርተ-ጥቅስ ውስጥ ማድረጌ ሰውየው ከናባቱ መጠሪያው የጫካ ስም - የተወረሰውም በምግባርም በአምሳልም እሱን ከማይመስል ሰው መሆኑን ሁላችሁም ታውቃላችሁ በሚል ግምት ነው - መንጌ እንኳ እናቱ ባወጡለት ስም ፀንቶ የቆመ ለመሆኑ አይጠረጠርም።

የ’በረከት’ን ስም ሳስብ በልጅነቴ ያሳቀኝን አንድ አጋጣሚ ያስታውሰኛል -

ነገሩ እንዲህ ነበር፦ ‘ካሳ ቀበሮ’ እያለ ሁሉም የሚጠራቸው የሰፈራችን አዛውንት የተለመደውን ቀማምሰው ወደቤታቸው ሲያዘግሙ ለወፍ መያዣ ብለው የመንደሩ ልጆች ያጠመዱት የገመድ ሸምቀቆ ጠልፏቸው ክፉኛ ይወድቃሉ - አካባቢው የነበረ ሁሉ አፈስፈስ አድረጎ ቀና ሲያደርጋቸው… “ለመሆኑ ይህን ጠላፊ ገመድ እዚህ የጣለው ማነው” በማለት ንዴት በተቀላቀለበት ስሜት ሲጠይቁ “እሱማ አቢይ ነው” የሚል መልስ ያገኛሉ “አቢይ አልከው? ምኑን አቢይ ሆነ እቡይ ነህ በለው” በማለት የሰፈሩን ሰው ሁሉ አሳቁን - አቢይ ዛሬ ትልቅ ሰው ሆኖ ባንድ የአፍሪካ አገር ዩንቨርሲቲ የበቃ መምህር ሆኗል።

ታዲያ ‘ስምኦን’ ብሎ ራሱን የሚጠራው ነብሰ-በላ ወያኔ አገር ላይ የሚፈፅመውን ግፍ ካሳ-ቀበሮ ቢሰሙ ‘ምኑን ‘ስምኦን’ ሆነ ‘ስመሞት’ በለው’ ማለታቸው አይቀርም ነበር ለማለት ነው።

‘ስምኦን’ እና መንግስቱ በግዜ ፣ በቁመና የሚለያዩ ነገርግን በኢትዮጵያ ህዝብ የቅርብ ታሪክ ውስጥ ለተፈፀሙ ዘግናኝ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መሪ ተዋናይ በመሆን የሚጠቀሱ ሰዎች በመሆናቸው እጅግ የሚመሳሰል ስብዕና እንዳላቸው ብዙዎች ይስማማሉ። በረከት ታጋይ ነበር ሲሉ ያስቀኛል - አንድን አምባገነን ከስልጣን ለማውረድ መታገል የዕድሜ ልክ አምባገነን መሆኛ ፈቃድ (እንደ መንጃ ፈቃድ) ነው ካልተባለ በስተቀር ‘ስምኦን’ እና መንግስቱ እንድም እና ሁለትም አምባገነን ናቸው። እንዴት ቢሉ …

ሁለቱም የፖለቲካ ‘ወሮበሎች’ ናቸው። ወሮበላ ማለት በጉልበቱ ሌሎችን እያስፈራራ ፣ እየቀማ የሚኖር ማለት አይደለም? እንግዲያውስ ሁለቱም ስልጣን ላይ የመጡትም ሆነ የቆዩት በጠመንጃ እና ደም በማፍሰስ ነው። ሁለቱም ለስልጣናቸው ቀናኢ ፣ ለተቀናቃኞቻቸው’ (አብሮ የቆየ ጓድ ቢሆን እንኳ) ‘ረመጥ’ ብሎም ከነሱ የተለየ አመለካከት ያለው ሁሉ ደመኛ ጠላት ነው ብለው የሚያስቡ ከመሆናቸው አኳያ እጅግ ይመሳሰላሉ። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሁለቱም አይናቸውን በጨው ያጠቡ ቀጣፊ መሆናቸው በጣም ያመሳስላቸዋል - ይሉኝታ ቢስ እና ስነምግባር እጅጉን የሚጎድላቸው ፍጡራን ናቸው።

ደግሞም ስለ ዲሞክረሲ እና ስለ አገራዊ ፖለቲካ ምርጫ ስርዓት ያላቸው አመለካከት ተመሳሳይ መሆኑን ስናጤን ተወራራሽ ባህሪያቸው ጠንካራ መሆኑን እንረዳለን። ለኮለኔል መንግስቱ ምርጫ ‘ከአብዮታዊ መሪያችን ጋር’ ወደፊት የሚለውን መፈክር አለመቃወም ማለት ሲሆን ለ’በረከት’ ደግሞ ‘አብዮታዊ ዲሞክረሲ’ የተሰኘውን የወያኔ ሰነድ አለመቃወም ሆኖ እናገኘዋለን። ሁለቱን መፈክሮች በሁለቱ አገዛዝ ዘመናት ተቃውሞ መቆም በአገር ክህደት እና አሸባሪነት የሚያስከስስ ከመሆኑም በላይ እስከ ሞት በሚያደርስ ሲያስቀጣ ቆይቷል።

የሞት ቅጣት - ድሮ በ‘አድሀሪ’ነት ዘንድሮ በ‘አሸባሪ’ነት።

መፅሀፍ የፃፉት አገር የገዙ እና በመግዛት ላይ የሚገኙ ሰዎች ናቸው። በመፃህፍታቸው ሁለቱም ስለ ስልጣን ዘመናቸው ትዝታ ፣ የስልጣን እርካብ ለመቆንጠጥ ያጋጠማቸውን ፈተና ብሎም ስለ አገር እና ህዝብ ያላቸው ግምት እና እምነት ምን እንደሚመስል የነገሩን በመሆኑ መፅሀፋቸው ጠቃሚ ነው። በየጓዳው እና በሚቆጣጠሩት መገናኛ አውታር የሰበኩትን እና የሚሰብኩትን በመፅሀፍ መልክ ጠርዘው በማቅረባቸው ብዙ አዲስ ነገር ባያነግሩንም አሁንም ማንነታቸውን በማያሻማ መልክ ይበልጥ እንድንገነዘብ የሚረዳ ዋቢ ሰነድ ከማበርከታቸው አኳያ ተጠቃሚዎች መሆናችንን ልንገነዘብ ይገባል።

*መንግስቱ እና በረከት ካለ መርማሪ ፖሊስ ቃላቸውን በውዴታ እና በመፅሀፍ መልክ ሰጥተዋል። አጋጣሚው ከፈቀደ ነገ ደግሞ በህግ ፊት እስከ ዛሬ ስለ ፃፉት እና ስላልፃፉትም ጭምር ማብራሪያ የሚሰጡበት ብዙ ጥያቄ እንዳለ እና ለዚያም እንዲሚበቁ እምነቴ ነው። በመፅሀፍታቸው ማንም ሌላ ሰው ሊነግረን የማይችል ጥቃቅን ጉዳይ ሳይቀር አንስተው ያወጉን በመሆኑ አገሪቱ በምን አይነት ግለሰቦች እጅ ወድቃ እንደቆየች እና አሁንም እንዳለች ይበልጥ እንድናውቅ ይረዳል።*

*በመግቢያዬ ላይ ጠቆም እንዳደረኩት የመጣጥፌ አላማ መፅሀፍቶቹን ለመገምገም አይደለም - እውነቱን ለመናገር አላነበብኳቸውም - በቅርብ ግዜ የማንበብ ጉጉትም የለኝም። ለምን ቢሉ - መጽሀፍ  የዕውቀት ምንጭ ነው ብዬ አምናለሁ ፤ መጽሀፍ የመንፈስ ምግብ ነው ብዬም በክብር እቀበላለሁ - መጽሀፍ የስነ-ጽሁፍ ጥበብ የወለደው ዘርፍ እንደ መሆኑ የህይወት እና የውበት መግለጫ ነው።*

*እንግዲህ አስቡት በውሸት እና በፕሮፓጋንዳ የታጨቀ ፤ ጥላቻ ፣ ዘረኝነት ፣ እብሪት እና ተራ ስድብ እንደ አንበጣ በወረረው ሰነድ ውስጥ ዕውቀትን እንዴት ይገበያሉ? እንዴትስ ንፁህን ዜጎችን ያለርህራሄ ከጨፈጨፉ ጣቶች ውበት እና ህይወትን እንሻለን? ታማኒነቱ በተሟጠጠ ግለሰው ተጽፎ ለንባብ የቀረበ መፅሀፍ እንዴት ሆኖ የዕውቀት ምንጭ ፣ እንዴትስ ሆኖ የውበት እና የጥበብ መግለጫ ይሆናል?*

*‘ስምኦን’ ሊያወጋን የከጀለው ምርጫ ያ የምናውቀው ፣ እኛው እራሳችን ተዋናይ ሆነን እነ ሺብሬ ደሳለኝን የገበርንበት ምርጫ አይደለም? ‘ስምኦን’ ሊያወጋን የተነሳው አቅመ አዳም ያልደረሱ ወጣቶች ፣ እናቶች በአጋዚ ጥይት ስለተቆሉበት ምርጫ 97 ነው ወይስ ሌላ? መላው ዜጋ የወያኔ አገዛዝ በቃ ብሎ በሰላማዊ ድምፅ ስለጠየቀበት ምርጫ ነው ሌላ?*

*‘ስምኦን’ ሊያወጋን የተነሳው በዝረራ ስለወደቀበት የቡግና ወረዳ ምርጫ ነው ሌላ?*

*መጽሀፍቱን አንብበው ግምገማዊ አስተያየታቸውን ያስነበቡን ወገኖች ብዙ ብለዋል። እኔ ለዚያ አልበቃሁም።*

*ግን ግን እውን ስለ ምርጫ 97 ከጨፍጫፊው በረከት ስምኦን ወግ የሚጠብቅ ኢትዮጵያዊ አለ?*

*በምርጫ 97 ዘመን ያልተወለደ ዛሬ ስባት ዓመት የሆነው ህፃን በወቅቱ ስለሆነው እና ስላልሆነው ለመረዳት ጉጉት ቢያድርበት ወግ ፍለጋ የሚሄደው በረከት ስምኦን ዘንድ ሳይሆን የሺብሬ ደሳለኝ እናት ዘንድ ነው ብዬ አምናለሁ። ምርጫ 97 በሉት 66 አብዮት በወቅቱ የህዝብን ፍላጎት ባኮላሹ ወይንም የህዝብን ድምፅ በሰረቁ እና ህዝብን በጨፈጨፉ ተዋናዮች ለመነገር የሚመች ወግ አይደለም።*

*ህዝብ ስለራሱ ወግ ሲያምረው የሚያወጋው ከነበረከት ጋር አይደለም - እነሱማ በጥይት አውግተውት ወግተውትስ የለ?*

*ይሁንና በረከት ስምኦን - ‘እነሆ ስለፈፀምኩት ጭፍጨፋ ጥቂት ላውጋችሁ’ ብሎናል።*

*እኔ በበኩሌ ‘ወግ ወጉንማ እነ ሽብሬ ደሳለኝ ቀድመው አውግተውናል - ጥሩ አድረገው ፣ እንዳንዘነጋው አሳምረው አውግተውናል።’ እላለሁ*

*ለመሆኑ በረከት እና መንግስቱ ልዩነት አላቸው? እንዴታ - መንግስቱ ተጀምሮ እስኪያልቅ ኢትዮጵያዊ ነው -*

*በረከትስ? እሱማ ጎንደር ያደገ ኤርትራዊ ነው - ያውም የአማራ ድርጅት መሪ። አቶ መለስ ዜናዊ ‘በቅድሚያ ትግራይ ከዚያ ኢትዮጵያዊ ነኝ’ ያለውን ስሌት ከተጠቀምን ደግሞ በረከት በቅድሚያ ኤርትራዊ ከዚያ አማራዊ ከዚያ ኢትዮጵያዊ ይሆናል ማለት ነው - ኢትዮጵያዊነትን ሶስተኛ ደረጃ ላይ በሚመጣ ማንነት ለብሶ ስለ ኢትዮጵያ ህዝብ ወግ ማውጋት ምን ያህል እንደሚዋጥላችሁ አላውቅም።*

*በረከት መፅሀፍ ላይ ቆሜ ሌላ መፅሀፍ ተንጠራርቼ ለማውረድ ይጠቅመሀል ካላችሁ እንስማማለን - ለግዜው ግን የዚያን ጨፍጫፊ መፅሀፍ ከመሬት ላይ አንስቼ የማንበብ አፒታይት እንደሌለኝ ላረጋግጥላችሁ ወዳለሁ።*